# የቀረጥ ተመላሽ ገንዘብዎ ከተወሰደብዎት

**WHEN THEY KEEP YOUR TAX REFUND**

**ገቢ መያዝ ምንድነው?**

የስቴት ወይም የካውንቲ ዕዳ ካለብዎት፣ የሚነሶታ ስቴት የቀረጥ ክፍል፣ የደሞዝ ወይም ሌላ ሃብት የቀረጥ ተመላሽ ገንዘብዎን ሊወስድ ይችላል። የቀረጥ ክፍሉ፣ ተመላሽ ገንዘብዎ ዕዳ ወዳለበት መስርያ ቤት ይልካል፤ ይህ " ገቢ መያዝ " ይባላል። ይህ ገንዘብ፤ ትርፍ ለተከፈለ የእርዳታ ገንዘብ፣ ለወረዳ ወይም የከተማ ሆስፒታሎች ወጪ፣ ለትምህርት ብድር፣ ለሕጻን እርዳታ፣ ለቅጣትና ለወንጀል ካሳ መክፈያ ነው።

**ተመላሽ ገንዘቤ ከመወሰድ የሚድነው መቼ ነው?**

ዕዳ ቢኖርብዎትም፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ከሆኑ፣ ተመላሽዎ አይወሰድም፤

- ዕዳዎ የህክምና ከሆና፤ በታከሙበት ጊዜ ገቢዎ ከተወሰነ ገንዘብ በታች ከሆነ። ደረጃው በያመቱ ይቀየራል። ለምሳሌ፤ የሕክምና ወጪዎ የ2000 ዓ.ም. ከሆነ፤ የ2000 ገቢዎ፤
    - ከ$8,800 በታች (ላንድ ሰው)
    - ከ$11,270 በታች (ካንድ ጥገኛ)
    - ከ$13,330 በታች (ከ 2 ጥገኛ)

  ሌላ ዓመቶችና፣ ከሁለት ጥገኞች በላይ ለማወቅ ከፈለጉ፣ የስቴት የገቢ ክፍልን በ651-296-3781 ደውለው ይጠይቁ።

- ዕዳው፤ ለተከፈልዎት ትርፍ፣ የሕዝብ እርዳታ ገንዘብ፣ መክፈያ ነው። ይህ የሚመጣውም፤ እንደ ኤም-ኤፍ-አይ-ፒ፣ ጂኤ፣ የመሰሉ የሕጻን አገልግሎቶች ነው። አሁን እርዳታ እያገኙ ቢሆንም፤ በመዋሸት ትርፍ አግኝተው ከነበረና የፕሮግራሙ ሕጎችን በማወቅ ካፈረሱ ነው።

- ከድርጅቱ ጋር የዕዳው መክፈል ፕሮግራም ካልዎት። መክፈሉን ካላቋርጡና፣ድርጅቱ ገንዘቡ እንዲያዝ አልፈልግም ካለ።

- ዕዳዎ ከስድስት ዓመት በላይ ከሆነ። የዚህ ሕግ የተለያየ ነው። ለምሳሌ፤ የትምህርት ዕዳ ከሆነ፣ 6 ዓመት ቢያልፍም ያስቆርጣሉ።



እላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ ተመላሽ ገንዘብዎ አይወሰድም። ነገር ግን በጽሑፍ ማስታወቅ አለብዎት።

**ምን ማስጠንቀቅያ አገኛለሁ?**

*መጀመርያ፤ የስቴት ወይም የካውንቲ ድርጅት፡ የስቴት የገቢ ክፍል ተመላሽዎን እንዲወስድ ይጠይቃል። ዕዳ አለብዎት የሚለው ድርጅት፡ በ 5 ቀኖች ውስጥ፡ መብትዎን የሚመለከት ማስታወቅያ ይልክልዎታል።*

*ማስታወቅያው የሚከተለውን መንገር አለበት፤*

- ዕዳው ለምን እንደሆነ፡ ብዛቱና መቼ እንደተደረገ፡
- ተመላሽዎን መውሰድ እንደፈለጉ፡
- ዕዳውና ማስቀረቱን መቃወም እንደሚችሉ፡
- የሚወሰደው ተመላሽ እንዴት እንደሚከራከሩና፡
- አቤቱታ ማቅርብ እንደሚችሉ።

**የአቤቱታው ጉዳይ የሚሰራው እንዴት ነው?**

ለድርጅቱ ዕዳ እንዳለብዎት በጽሑፍ ያስታውቁ። **ለገቢው ክፍል ሳይሆን።** በደብዳቤው አርእስት "ገቢ መያዝ አቤቱታ" መሆኑን ያስታውቁ። ባጭሩ ገንዘቡን ማስቀረት እንዳልነበረባቸው ያስታውቁ።

ምክንያቶቹ ከሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፤

- ዕዳ የለብዎትም ወይም
- ዕዳ ቢኖርብዎትም በሕግ ምክንያት እርስዎን እንደማይመለከት
  (ላይ ያለውን ይመልከቱ)።



**የደብዳቤው ቅጂ ይያዙ።** ድርጅቱ ደብዳቤው ከላከበት ቀን ጀምሮ በ45 ቀኖች ውስጥ መልስ ማግኘት አለበት። በ30 ቀኖች ውስጥ ድርጅቱ አቤቱታውን መስማት አለበት። ጠበቃ አያስፈልግዎትም። ሆኖም በስልክ አንዱን ማናገር ጥሩ ነው።

የዕዳው መክፈል ውሳኔ በፍርድ የተወሰነ ወይም የተሰጠ ትዛዝ ከሆነ፡ የአቤቱታ የመሰማት መብት የልዎትም።

ከድርጅቱ የመብቶች መስማት ማስታወቅያ ባያገኙም፡ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

- ለድርጅቱ የይግባኝ ደብድቤ ይጻፉ።
- የ45 ቀኑ መልስ መስጠት ከድርጅቱ፡ ገንዘብዎን መውሰድ እንደፈለገ የሚነግር በብዳቤ እስካገኙ ድረስ አይቆጠርም።
- ድርጅቱ ደብዳቤ ልኬ ነበር ካለና፡ ካልደረስዎት፤ በሁለት ጉዳዮች አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ። መጀመርያ፤ ማስታወቅያው በእውነት ደርስዎታል ወይ? ሁለተኛ፤ ተመላሽ ገንዘብዎን ሊወስዱ ይችላሉ ወይ?

**Minneapolis Legal Aid – CLE**
*MN Legal Services Coalition*
*2324 University Avenue, Suite 101B*
*St. Paul, MN 55114*

*ይህ ማብራርያ ወረቀት አንድ ዓመት ካለፈው አይጠቀሙበት። የማብራርያ ወረቀቶች ዝርዝር፡ የተሻሻለ ወይም የተቀየረ ሌላ ዘዴ ከፈለጉ ይጻፉልን። የማብራርያ ወረቀቶች፡ ለሕግ ችግሮች ሙሉ መፍትሔ ስላልሆኑ፡ ጠበቃ ያማክሩ።*

© 2011 Mid-Minnesota Legal Assistance. This document may be reproduced and used for non-commercial personal and educational purposes only. All other rights reserved. This notice must remain on all copies. Reproduction, distribution, and use for commercial purposes are strictly prohibited.